# ኃጢአት እና ንሰሃ

## ኃጢአት

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጥያት በተለያዩ መንገዶች ተፅፈው እናገኛለን ።

1. ሐማርቲያ፦ (ሀጥያት)። ፣ ሐማርቶሎስ፦ ደግሞ ሀጥያተኛ ። ፣ እና ሀማርተነው፦ ደግሞ ሀጥያትን ማድረግ ነው ። እነዚህ ቃላት የሚያሳዩት ወደታቀደለት አለማ አለመድረስን ነው ። አንድ ቀስተኛ በተዘጋጀለት ሰርክል ውስጥ ያለችው ነጥብ ላይ ካልሰካ ሐማርቲያ ይባላል ። ሳተ ወይንም ግቡን አልመታም እንደማለት ነው ።

2ኛ, አድኪያ ፦ ይህ አመፅ የሚለውን የሚያመለክት ቃል ነው ። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መሰፈርት ሰጥቶ የሰው ልጅ ከእዚህ መለኪያ ጋር አለመሰማማቱን የሚያሳይ ነው ።

3ኛ, ታራፕቶማ ፦ ይህ ደግሞ መተላለፍን የሚያመለክት ነው ። ይህም ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው መንገድ ለቅቆ በሌላ መንገድ መራመዱን የሚያሳይ ነው ።

4ኛ, አኖሚያ ፦ (አመፅ) ማለት ነው ። ይህም ያለ ህግ ወይንም ከህግ ውጪ መኖርን የሚያመለክት ነው ።

5ኛ, ኦፋይሊቲስ ፦ (እዳ ያለበት) ማለት ነው ።

በእነዚህ ሁሉ መንገድ ሰዎች እግዚአብሔርን መበደላቸው መፅሀፍ ቅዱስ በግልጽ ያሰተምራል ።

ኃጢአት ገዳይ በሽታ ነው ፣ ነፍስህን እስኪበላው ድረስ አይለቅም። ኃጢአት ራሱ ገሃነም ነው ፣ እግዚአብሔርን ያዋርዳል ፣ እግዚአብሔርን ያሰቆጣ ። ኃጢአት እንዳናደርግ የተከለከልነው በጥሩ ምክንያቶች ነው። ስለዚህ በኃጢያአታችን እንጸጸተ። ምክንያቱም ኃጢአትን ስንሠራ የእግዚአብሔርን ሕግ እየጣስን ፍቅሩንና ምሕረቱን እየተሳደብን ነው ። ኃጢያትን መስራት - እንዲሁ ተራ ፍራት ብቻ እና እራስን የማቅለል ስሜት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ኃጢአት መሥራት ያድነን ዘንድ አንድ ልጁን በቸርነቱ የሰጠንን አፍቃሪ አምላክን ማሳዘን ነው ። ብዙ ውለታ ያደረገልንን እረኛችንን እናሳዝናለን። በጥልቀት በልባችን ያደረግነውን እንጸየፍ እና እንጸጸት። የሠራነውንም ኃጢአት ለትሑታን አምላክ እንናናዘዝ። መንገዳችንንም ከጥፋት መንገድ ወደ እግዚአብሔር በማዞር ቅንነታችንን እናሳይ። በእርሱ እንድንኖር እራሳችንን ከኃጢአት እናፋታ ፣ እና ንሰሀ ለመግባት ወደ ኋላ እንበል። ክርሰቶሰ ያልሞተለት ኃጢአት የለም።

ሰዎቸ ለዓለም ጀርባቸውን ሰጥተው ወደ እርሱ ከተመለሱ ክፉዎችን ለመቀበል እጁ ሁል ጊዜ ክፍት ነው። የንስሐ አባትና ወዳጅ ነው። ኃጢአታችን በጣም ከባድ ቢሆንም - ይቅርታ የማይደረግልን ግን ንሰሐ አለመግባታችን ነው። ንሰሐም ባለመግባት ሌላ ከባድ ኃጢአት አንጨምር። ወደ ክርሰቶሰ እንሂድ ወደ ደሙ እንጠጋ ፣ እርሱም ኃጢአታችንን ያነጻል። ከመንፈሰ ብርታት ለማግኘት እንጸልይ እና በቅዱስ ቃሉ ራሳችንን እናጽናና።

# ንሰሐ

መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ንሰሐ የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም በግሪኩ to change mind  አዕምሮን መቀየር ፣ አስተሳሰብን መለወጥ ። በዕብራይስጡ የቃሉም ትርጉም turning around. በቀጥታ መዞር ፣ መንገድ መቀየር ነው ። ወደ ምስራቅ ከነበርንበት ወደ ምዕራብ 180 ዲግሪ መዞር ነው ። ለእግዚአብሔር ጀርባ ሰጥተን ከነበረ ወደ ፊቱ 180 ዲግሪ መዞር  ነው ።  እውነተኛ የመፅሐፍ ቅዱስ ንሰሐ ከመፀፀት ወይንም ከመከፋት በላይ ነው ። in fact this is part of repentance. Repentance is not emotion. Repentance is decision.  አዲስ ኪዳን ላይ ሜታኖኦ የሚለውን ግስ ይጠቀማል ። ሜታኖኦ ማለት ከእውቀት በኋላ የተገኘ ሆኖ አዕምሮን እና አላማን መለወጥ ማለት ነው ።

ንሰሐ ያለፈን ሰህተት እንደሆነ ማወቅ እና ወደፊት በትክክል ለማሰብ መወሰንን ያካትታል ። ንሰሐ የገባ ሰው ቀደም ሲል ሰለተቀበለው አስተሳሰብ ሁለተኛ (ተለዋጭ ) ሀሳብ አለው ። ሰለ እግዚአብሔር ፣ ሰለ ሀጥያት ፣ ሰለ ቅድሰና እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የአመለካከት ለውጥ ፣ አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ አለው ። ንሰሐ እግዚአብሔር የሚሰጠን ነገር ነው ። ሐዋ 5:31-   11:18።

በአጭሩ ንሰሐን ለመረዳት ሀጥያትን መረዳት ወሳኝ ነው ።  ከኃጢያት ማለት (አመፅ)  ወይንም missing the mark ማለት ሲሆን - Repentance ደግሞ ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለሰ ነው ።

**አዘጋጅ ፦ ተካልኝ ኃ/ሚካኤል**